የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴሬሽን ምክር ቤት

The House of Federation
of
The Federal Democratic Republic
of Ethiopia

ቁጥር
No. ኤፍ.ሞ/ፍ.ሪ/5/1195

ቀን
Date. 9/11/2016

ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

<u>አዲስ አበባ</u>

ለእነ አቶ ወንድሙ ተሊላ (2 ሰዎች)

<u>ባሉበት</u>

ጉዳዩ፡-<u>የምክር ቤቱን ውሳኔ ስለማሳወቅ</u>

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በ.ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 62 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በአንቀጽ 83 ንዑስ አንቀጽ 1 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሕገ መንግስታዊ ክርክር ሲነሳ ሕገ መንግስቱን በመተርጎም ውሳኔ ይሰጣል፡፡

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር ለመዘርዘር በወጣው አዋጅ ቁጥር 1261/2013 አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 80 መሰረት ምክር ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና አስገዳጅ መሆኑን እንዲሁም ማንኛውም ሰው የፌዴራል የክልል ፍርድ ቤቶች፣ የፌዴራልና የክልል መንግስታት፣ የመንግስት ባለስልጣናት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት የምክር ቤቱን ውሳኔ የማክበር የማስፈጸምና የመፈጸም ግዴታ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሰኔ 25 ቀን 2016 ዓ.ም 6ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 3ኛ ዓመት 2ኛ መደበኛ ጉባዔ እነ አቶ ወንድሙ ተሊላ (2 ሰዎች) ባቀረቡት የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ላይ ከፌዴራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የቀረበውን ውሳኔ ሀሳብ ተመልከቶ የሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ 11 ገጽ (አስራ አንድ) ገጽ ከዚህ መሸኛ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ የተላከላችሁ ሰለሆነ በምክር ቤቱ ውሳኔ መሰረት እንዲፈጸም አስታውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

አገኘሁ ተሻገር ገሠሠ
የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ

<u>ግልባጭ</u>፣

- ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ
  <u>አዲስ አበባ</u>
  <u>በፌዴሬሽን ም/ቤት</u>
- ለሕገ መንግስት ትርጉምና ውሳኔ አፈፃፀም ክትትል ቋሚ ኮሚቴ
  <u>በፌዴሬሽን ም/ቤት ጽ/ቤት</u>
- ለሕገ መንግስት ትርጉም እና የሕጎች ሕገ መንግስታዊነት ክትትል ዳይሬክቶሬት

ስልክ: 011-1-223322 ፋክስ: 011-1-242304 E-mail:hofethiopia@gmail.com ፖ.ሣ.ቁ. 20212/1000
Tell.011-1-242303/01 Fax: 011-1-241208 Web Site:http:/www.hofethiopia.gov.et P.o.Box
Addis Abeba አዲስ አበባ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 6ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 3ኛ የሥራ ዓመት 2ኛ መደበኛ ጉባዔ ሰኔ 25 ቀን 2016 ዓ.ም

የመዝገብ ቁጥር 120/16

አመልካቾች፡- እነ አቶ ወንድሙ ተሊላ (2 ሰዎች)

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አሰገደች በላይ

የፌዴሬሽን ምክር ቤት የአጣሪ ጉባኤ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ላይ መርምሮ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

<u>የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ እና የውሳኔ ሀሳብ</u>

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 25/05/2010 ዓ.ም ለጉባኤው ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ሲሆን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄው የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ ይከፈለኝ በሚል ነው፡፡

ጉዳዩ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍ /ፍ/ቤት በመ/ቁ 24665 ፣ በኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት መ.ቁ 257819 በኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 262353 እና በፌደራል ጠ/ፍ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/150205 ላይ ውሳኔ ያገኘ ጉይ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በዞኑ ከፍ/ፍ//ቤት ሲሆን አመልካቾች ከሳሾች ነበሩ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡

አመልካቾች በክሳቸው ላይ ከተጠሪ ጋር በቀን 27/10/2006 ዓ.ም ባደረግነው የጥብቅና አገልግሎት ስምምነት ውል ተጠሪ በሚስትነት ማግኘት የሚገባቸውን እና ልጆቻቸው በወራሽነት ከሚያገኙት 10% ሊከፍሉን ተስማምተንና የቅድሚያ ክፍያ ብር 10,000.00 (አስር ሺህ) ተከፍሎን እስከ ክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ወክለናቸው ክርክር ካሄደን አልቋል፡፡

ተጠሪ ጉዳያቸውን በውሉ ስምምነት በመጨረስ ለክርክሩ መነሻ ከሆነው ንብረት ውስጥ የራሳቸውን እና የልጆቻቸውን የውርስ ድርሻ በአዳማ ከተማ ቀበሌ 09 የሚገኝ ቤት በ 442 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ያለ ብር 4,000,000.00 (አራት ሚሊዮን) የሚገመት ባለ 7 ክፍል ቤት አግኝተዋል፡፡

ሆኖም በስምምነታችን መሰረት ለአገልግሎታችን ብር 200,000.00 (ሁለት መቶ ሺህ) ክፍያ እንዲሰጡን ብንጠይቅ ፍቃደኛ ስላልሆኑ በውሉ መሰረት ይህን ገንዘብ ከህጋዊ

ሆኖም አመልካች ክፍያውን በሚመለከት ክፈይ ከተባልኩም ባገኘሁት ንብረት ግምት መሰረት መሆን አለበት በማለት ተከራክረው እንደነበር የስር ፍ/ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡

የስር ፍ/ቤቶች በዚህ ላይ ውሳኔ ከመስጠታቸው በፊት ተጠሪ አግኝተውታል የተባለው ባለ 7 ክፍል ቤት በእውነት ግምቱ ብር 4,000,000.00 (አራት ሚሊዮን) ያወጣል ወይስ አያወጣም ? የሚለውን በሚመለከተው ባለሙያ አጣርቶ በሚቀርበው ውጤት ላይ በመመርኮዝ መወሰን ሲገባቸው በአመልካቾች የቀረበውን ግምት ብቻ ተቀብለውና የቀረበውን ተቃውሞ ወደ ጎን በመተው የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበትና ሊስተካከል የሚገባ ነው ሲል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348 መሰረት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ላይ ያላቸውን አቤቱታ ለፌዴራል ጠ/ፍ/ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ችሎቱ ለሰበር አያስቀርብም በማለት መዝገቡን በትዕዛዝ ዘግቶታል፡፡

አመልካቾች በክልልና በፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለጉባዔው ባቀረቡት አቤቱታ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በታች ፍ/ቤት በተረጋገጠው መሰረት ጉዳዩ በማንኛውም መልኩ ቢጠናቀቅ አመልካቾች ሊያገኙ የሚገባውን የአገልግሎት ክፍያ አያስቀረውም ተብሎ መወሰኑ አግባብ መሆኑን ገልፆ፣ ነገር ግን በሌላ በኩል ደግሞ በክፍያ መጠን ረገድ የስር ፍ/ቤት አመልካቾች ያቀረቡትን የዋጋ ግምት ያለአንዳች የባለሙያ ማስረጃ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈፅሞበታል ሲል በመሻር እርስ በእርሱ የተቃረነ ሁለት ትርጉም ያለው ውሳኔ መስጠቱ አግባብ አይደለም፡፡

እንዲሁም ተጠሪ በአማራጭ ባቀረቡት ክርክር ከከፈሉም ባገኙት ንብረት መጠን ልክ ለመክፈል ተስማምተው እያለ ክፍያውን እንዳይከፍሉ ፍርድ መስጠቱ ተገቢነት የለውም፡፡

በሌላ በኩል የታች ፍ/ቤት በክፍያው መጠን ላይ የሰጠው ፍርድ ተገቢነት የለውም ቢባል እንኳን የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔውን ለሰጠው ፍ/ቤት መልሶ እንዲጣራና እንዲስተካከል መወሰን ሲገባው ፍርዱን ሙሉ በሙሉ መሻሩ የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ በተመሳሳይም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ማረም ሲገባው አያስቀርብም ሲል መዝገቡን መዝጋቱ የሕገ መንግስቱን አንቀፅ 25 ፣33 (2)፣ 37 የእኩልነት፣ ፍትህ የማግኘት እና ዜግነታቸው በህግ ሊሚያስገኘው መብት ጥበቃና ጥቅም የማግኘት

መብቶቻቸውን እንደሚጥስና መብታቸውን ሙሉ በሙሉ እንደሚነፍግ ገልጸው እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የአመልካቾችን የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ለማጣራትና ፍትሃዊ ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሃሳብ ለማቅረብ እንዲረዳ ተጠሪ በጉዳዩ ላይ ምላሽ እንዲሰጡ የሚከተሉትን መነሻ ጭብጦች በመያዝ መልስ እንዲሰጡ አድርጓል፡-

ውሳኔው በሕገ መንግስቱ በአንቀፅ 41 (1) አመልካቾች በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ የመሰማራትና ለመተዳደሪያቸው የመረጡትን ስራ የመስራት እና ጥቅም የማግኘት መብታቸውን ይጥሳል ወይስ አይጥስም ?

እንዲሁም በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40 አመልካች የተጠበቀላቸውን በባንዘባቸው፣ በጉልበታቸው ወይም በእውቀታቸው ያፈሩትን የንብረት መብት ጥሷል ሊባል ይችላል ወይስ አይችልም ? ለምን? የሚሉት ናቸው፡፡

ተጠሪ መልሳቸውን እንዲያቀርቡ የጉዳዩን አመጣጥና የአመልካቾችን አቤቱታ የያዘ መጥሪያ ደርሷቸው በቀን 06/13/2015 ዓ.ም መልስ አቅርበዋል፡፡

በመልሳቸውም ከአመልካቾች ጋር የጥብቅና ስምምነት ማድረጋቸውን፣ የጥብቅና ውል አገልግሎት አከፋፈል መርህ መታየት ያለበትም ጉዳዩ የወሰደውን ጊዜና የሚጠይቀውን ድካም እና የጉዳዩን ውስብስበነት ታሳቢ ማድረግ እንዳለበት ገልፀዋል፡፡

ለዚህ አቤቱታ መነሻ ከሆነው ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሲመልሱ ጉዳዩ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 38088 በክርክር ላይ እያለን ሌሎች የሚች ባለቤታቸው ወራሾች በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ74626 ከሰዋቸውና የከፍተኛ ፍ/ቤቱን ክስ ገብተው አመልካቾች ፍ/ቤት ወደ ተመሰረተው ክርክር በማሳገዳቸው በወረዳው ሲከራከሩላቸው እንደቆዩ፣ ፍ/ቤቱም የተጠሪን ሶስት ልጆች ከአባታቸው ውርስ በመንቀል ለተጠሪና ለከሳሾች የመውረስ መብት ጠብቆ ድርሻ እንዲያገኙ መወሰኑን፣ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካቾች ለዞኑ ከፍ/ፍ/ቤት ይግባኝ ጠይቀው መፅናቱንም ገልፀዋል፡፡

ሆኖም አመልካቾች በውላቸው መሰረት በዚህ ውሳኔ ላይ እስከ ፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው መብታቸውን ማስከበር ሲገባቸው የወረዳውና የከፍ/ፍ/ቤቱ የሰጡትን የተሳሳተ ውሳኔ ተቀብለው ይግባኝ አለመጠየቃቸውን እና ይህም አግባብ

እንዳልሆነ ፣ ሆኖም ይህን ጉዳይ ከልጆቻቸው ጋር በአባት ከሚገናኝ ሌላ ወንድማቸው አቶ መላኩ ለማ ጋር በመነጋገርና ለክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 203691 አቤቱታ አቅርበው የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በማሻር ልጆቻቸው ወደ ውርስ እንዲመለሱ ማስወሰናቸውን፤ ከውሳኔ በኋላም ጉዳዩ በስምምነት ማለቁንና ድርሻቸውን መከፋፈላቸውን ጠቅሰዋል፡፡

በዚህ ውሳኔ ውስጥም ምንም የአመልካቾች ጥረት እና ድካም የሌለ መሆኑንና ውላቸውን በራሳቸው ማቋረጣቸውን እንደሚያሳይ ጠቅሰው ክርክሩን በራሳቸው ብቻ የፈፀሙና ጉዳዩም ከጀርባቸው በስምምነት እንዳለቀ በማስመሰል ያነሱት አቤቱታ ተቀባይነት እንደሌለው ተከራክረዋል፡፡

በአጠቃላይ አመልካቾች በታች ፍ/ቤቶች የተወሰነውን ውሳኔ በይግባኝ ወስደው ባላሻሩበት ሁኔታ ላልሰሩት ስራ ክፍያ መጠየቃቸውም ተገቢነት የሌለው መሆኑን፣ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ጥያቄያቸውን ውድቅ ማድረጉና የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ማፅናቱ ትክክል መሆኑን ገልፀው ጉባኤው በፍርድ ቤቶች ክርክር የተደረገባቸውንና ውሳኔ የተሰጠባቸውን መዝገቦች አስቀርቦ እንዲመለከትላቸውና የፍ/ቤቶቹን ውሳኔ እንዲያፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾች ለጉባኤው ያቀረቡት አቤቱታ ፍ/ቤቶች ከሰጧቸው ውሣኔዎች፣ ከተጠሪ መልስና ጉዳዩን ከሚመለከቱ ሕገ መንግስታዊ መብቶች አንፃር ተመርምሯል፡፡ ከጉዳዩ አመጣጥ ለማየት እንደተቻለው በግራ ቀኙ የተነሳውን የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ ክርክር የተመለከቱት የታች ፍ/ ቤቶች አመልካቾች ለተጠሪ የጥብቅና አገልግሎት መስጠታቸውን ማረጋገጣቸውንና በውላቸው መሰረት ተጠሪ አመልካቾች የጠየቁትን ብር 200,000.00 (ሁለት መቶ ሺህ) ሊከፍሉ እንደሚገባ ወስነዋል፡፡

የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የስር ፍ/ቤቶች ትክክለኛው የቤቱ ግምት ሳይጣራ አመልካቾች ባቀረቡት የንብረት ግምት ላይ ብቻ መሰረት በማድረግ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት እንደተፈፀመበት በመጥቀስ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ አመልካቾችም ይህ ውሳኔ የጥብቅና አገልግሎት መስጠታቸውን አረጋግጠና ክፍያ የማግኘት መብታቸውን ጠብቆ ክፍያውን አለመወሰኑ መብታቸውን በሙሉ

እንዳሳጣቸው የሚጠቅሱ በመሆኑ ጉዳዩ ፍትህ ከማግኘትና በመረጡት ስራ ከመሰማራትና ከስራው ከመጠቀም ጋር የተያያዘ እንደሆነ ለማየት ተችሏል፡፡

በመሆኑም የአመልካቾችን አቤቱታ ለመመርመር አንደኛ ውሳኔው የአመልካቾችን ፍትህ የማግኘት መብት ጥሷል ያስኛል ወይስ አያሰኝም? ሁለተኛ ውሳኔው በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያው የመረጠውን ስራ የመስራት ሕገ መንግስታዊ መብት ይጥሳል ወይስ አይጥስም? የሚሉትን ሁለት ጭብጦች መርምሯል ፡፡

በመጀመሪያው ጭብጥ ስር ውሳኔው ከአመልካቾች ፍትህ የማግኘት መብት ጋር ያለውን ግንኙነት ለመወሰን በቅድሚያ ለተያዘው ጉዳይ መነሻ የሆነው የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚችሎት የሰጠው ውሳኔ በህግ አግባብ የተሰጠ መሆን አለመሆኑን መመልከት ጠቃሚ ነው፡፡

ተጠሪ በስር ፍ/ቤቶች እንዲከፍሉ የተላለፈባቸውን ውሳኔ በመቃወም ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት የሚያሳየው አመልካቾች ውሉን ፈፅመዋል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለመሆኑ እና የጥብቅና ክፍያውን መክፈል ካለባቸውም ያገኙትን ጥቅም መሰረት ማድረግ እንዳለበት በመግለፅ ነው፡፡

ችሎቱም አቤቱታውን ለመመርመር የያዘው ጭብጥ በተመሳሳይ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት በነበራቸው ክርክር አመልካቾች ግዴታቸውን ስላልፈፀሙ ክፍያው እንደማይገባቸው፤ ክፍያውን ይክፈሉ ከተባለም ፍ/ቤቱ አስገምቶ በሚያስቀርበው ውጤት ላይ ተመስርቶ መሆን እንዳለበት እየጠየቁ የስር ፍ/ቤት ይህን አልፎ የሰጠው ውሳኔ የህግ ድጋፍ አለው ወይስ የለውም? የሚል ነው፡፡

ችሎቱ ፍርድ የሰጠው ውሳኔው ስለመፈፀም አለመፈፀሙና ይህን ተከትሎ የሚከፈል ክፍያ ስለመኖር አለመኖሩ አጣርቶ ክፍያ በአመልካቾች ግምት ላይ ብቻ በመመስረት ሊሰጥ እንደማይገባ በመግለፅ ነው፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ .182 በአንድ ፍርድ/ውሳኔ ሃተታ ላይ ስለሚሰፍሩ ነገሮች ያስቀመጠ ሲሆን አንድ ፍርድ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ዋነኛ ጉዳይ በአጭሩ የሚገልፅ ሆኖ

የተያዘውን ጭብጥ፣ እንዴት እንደተወሰነ እና የተወሰነበት ምክንያት መግለፅ እንዳለበት ያሳያል።

ድንጋጌው በይግባኝ የሚቀርቡ ጉዳዮችን በሚመለከትም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሚሰጠው ፍርድ ወይም ውሳኔ የስር ፍ/ቤትን ፍርድ ያሻሻለው ወይም የለወጠው እንደሆነ በትችቱ ላይ ለይግባኝ ባዩ የሚገባውን ዳኝነት ዘርዝሮ መግለፅ እንዳለበት ያስረዳል።

በተጨማሪም ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ነበር ብሎ በሚገምተው ጉዳይ ላይ የስር ፍ/ቤቱ አስተያየት መስጠት ወይም መወሰን ይገባው እንደሆነ ተገቢ መስሎ የታየውንና ነገሩን ለማስፈፀም ተስማሚ ነው ብሎ የሚገምተውን ማናቸውንም ሌላ ብይን ወይም ትእዛዝ ወይም ፍርድ መስጠት እንደሚችል በግልፅ አስቀምጧል።

ፍ/ቤቱ ከቀረቡለት ጭብጦች አንዱ ጭብጥ ቀሪዎቹን ጭብጦች ያጠቃልላቸዋል ብሎ ከገመተ በአንድ ጭብጥ መወሰን እንደሚችል፤ ሆኖም የቀረቡት ጭብጦች በየራሳቸው መወሰን የሚያስፈልጋቸው ሆነው ሲገኙ ስለ እያንዳንዱ ጭብጥ አወሳሰን የተሰጠው ምክንያት ሁሉ በትችት ላይ መገለፅ እንዳለበት ያሳያል።

በተጨማሪም የፍ /ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 183 በአንድ ውሳኔ እንደነገሩ ሁኔታ ውስጥ ስለሚገለፁ ጉዳዮች ሲዘረዝር በንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል "መ" ላይ "አንድ ነገር ከማድረግ እንዲወገድ ወይም የተወሰነ ገንዘብ እንዲከፈል፣ በትእዛዙ ላይ የተገለፀን ነገር እንዲፈፅም ወይም ከመፈፀም እንዲታገድ፣ የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲያስረክብ ወይም እንዲለቅ ... ሲል ፍርዱ በምን አግባብ እንደሚተገበር የሚገልፅ ግልፅ ትእዛዝ እንደሚያስፈልገው ጠቁሟል።

በያዝነው ጉዳይ ሰበር ሰሚ ችሎቱ የአመልካቾችን ጥያቄዎች ይዞ የመረመረ ሲሆን የችሎቱ ዋና የውሳኔ ክፍል እንደሚያሳየው በታች ፍ/ቤት አመልካቾች ውሉን መፈፀማቸውን በማረጋገጥ የተሰጠው ውሳኔ ጉድለት እንዳልተገኘበት ነው።

በሌላ በኩል ክፍያውን በሚመለከት ሲወሰን "አከራካሪው ቤት ብር 4,000,000.00 (አራት ሚሊዮን ብር) ያወጣል ወይስ አያወጣም ? የሚለውን ጉዳይ የስር ፍ/ቤቶች በባለሙያ አጣርተው በሚቀርበው ውጤት ላይ በመመርኮዝ መወሰን ሲገባቸው በአመልካቾች የቀረበውን ግምት መነሻ ብቻ ተቀብለው የተጠሪን ተቃውሞ ወደ ጎን በመተው የሰጡት

ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና ሊስተካከል የሚገባው ነው..." በሚል የተቀመጠ ነው፡፡

ይህም ተጠሪ ግዴታቸውን ሳይወጡ ከሕግ ውጪ ያቋረጡት ውል መሆኑንና በውላቸው መሰረት ክፍያን በሚመለከት ለአመልካቾች ሊፈፅሙ የሚገባ ግዴታ እንዳለ እንጂ ተጠሪ ለአመልካቾች የአገልግሎት ክፍያ ሊከፍሉ እንደማይገደዱ የሚያሳ አይደለም፡፡

ሰበር ሰሚ ችሎቱ የስር ፍ/ቤቶች በመጠኑ ላይ ተጠሪ እንዲከፍሉ የወሰኑበትን አግባብ ተችቶ እያለ በትእዛዝ ክፍሉ ውስጥ የዞኑን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች እንደተሻሩ በመጥቀስ የክርክሩ ዋና ትኩረትና ውጤት በሆነው የክፍያ ጉዳይ ላይ ግልፅና ቀጥተኛ ትእዛዝ ሳይሰጥ አልፎታል፡፡

ችሎቱ የክፍያውን መጠን በሚመለከት በራሱ መወሰን ሲችል ወይም በስር ፍ/ቤቶች በድጋሚ ታይቶና ተጣርቶ እንዲወሰን ትእዛዝ መስጠት ሲገባው በደፈናው በመሻር ያስተላለፈው ውሳኔ ነው፡፡

ይህም የችሎቱ ውሳኔ በፍትሐብሄር ሥነ ሥርዓት ሕጉ በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሰረት ፍ/ቤቶች ግልፅ ፍርድ ወይም ትእዛዝ እንዲሰጡ የሚያስገድዳቸውን ሕጋዊ አሰራር ያልተከተለና በውሳኔው አፈፃፀም ሂደት ላይ መሰረታዊ ችግር የሚፈጥር መሆኑን ያሳያል፡፡

ውሳኔው በሕገ መንግስታዊ ፍትህ የማግኘት መብት የመጣስ ውጤት የሚያስከትል መሆን አለመሆኑ ተመርምሯል፡፡ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 37(1) ላይ ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት ያለው መሆኑ ተደንግጓል፡፡

ይህ መብት በውስጡ ሰፊና ዝርዝር የመብት ዓይነቶችን የያዘ ሲሆን በአንድ ጉዳይ ላይ መብቴ ወይም ጥቅሜ ተነክቷል የሚል ሰው መብቱ ወይም ጥቅሙ ስለመነካቱ አቤቱታውን ሊያቀርብና ተገቢውን መፍትሄ ሊያገኝ የሚችልበት የህግ ስርአት መኖር እንዳለበት የሚያሳይ ነው፡፡

ይህም አንድ ሰው ጉዳዩን በፍ/ቤት የማቅረብ ፣ የቀረበበትን ማስረጃ የማወቅና የራሱን ማስረጃ አቅርቦ ራሱን የመከላከል መብት ላይ ብቻ የሚቆም ሳይሆን የሚሰጠው የፍርድ ጥራትንም የሚጨምር ነው፡፡

ይህም ፍ/ቤቶች ለቀረበላቸው ጉዳይ የሚሰጡት ፍርድ ወይም ትእዛዝ በበቂ ምክንያት የተደገፈ ፣ ለእያንዳንዱ ጭብጥ ግልፅ ፍርድና ውጤት ሊኖረው ወይም ሊፈፀም በሚያስችል መልኩ የተቀመጠ ትእዛዝን ያካተተ መሆን እንዳለበት ከላይ በሥነ ሥርአት ሕጉ በግልፅ ከተጠቀሱ ድንጋጌዎች አጠቃላይ መንፈስና ዓላማ መረዳት ይቻላል፡፡

የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍ/ቤቶች በጥብቅና አገልግሎት ክፍያው ላይ የሰጡትን ውሳኔ ሊስተካከል እንደሚገባ በዋናው የውሳኔ ክፍል ውስጥ ገልፆ መወሰኑ ተገቢ ቢሆንም በምን አግባብና በየትኛው ፍ/ቤት ተጣርቶ ሊወሰን እንደሚገባ የሰጠው ግልፅ ትእዛዝ/አቅጣጫ የለም፡፡ ይህም በፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አልተስተካከለም፡፡

ከዚህ የምንገነዘበው የክፍያ መጠኑን በሚመለከት ተቀባይነት ያገኘውን የአመልካቾች ክርክር የመጨረሻ ውሳኔ ሊያገኝ የሚችልበትን መንገድ ሳይጠቁም ያለፈ መሆኑን ነው፡፡

በመሆኑም የሰበር ሰሚ ችሎቶቹ ውሳኔ አመልካቾች በውል የተቋቋመላቸውንና በፍርድ ቤቶቹ የተረጋገጠላቸውን መብት እንዳይፈፀምላቸው፣ እንዲሁም ዳግመኛ ለፍ/ቤት አቅርበው እንዳይጠይቁና የመጨረሻ ፍርድ እንዳያገኙ ያደረገ በመሆኑ ውሳኔው የአመልካቾችን ሕገ መንግስታዊ ፍትህ የማግኘት መብት የጣሰ ነው፡፡

በአጠቃላይ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እና የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ አመልካቾች ከታች ፍ/ቤቶች ጀምሮ ተሟግተው በግራ ቀኙ መካከል ያለው ውል እንዲፈፀምና መብታቸው እንዲከበርላቸው የተሰጠውን ውሳኔ ውጤት እንዳይኖረው በሚያደርግ መልኩ የተደመደመ በመሆኑ ውሳኔው የአመልካቾችን ፍትህ የማግኘት መብት የሚጥስ ነው፡፡

በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አዳማ ልዩ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት መ/ቁ 24665 በቀን 06/06/09 ዓ.ም ተወስኖ በኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 25/78/19 በቀን 15/07/09 ዓ.ም የፀናውን ውሳኔ በመሻር የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 262353 በቀን 20/02/10 ዓ.ም እና የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 150205 በቀን 25/04/10 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ 1 የሚጥስ በመሆኑ ተፈፃሚ እንዳይሆን፡፡

የኦሮሚያ ክልል የአዳማ ልዩ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ የኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የጥብቅና አገልግሎት ክፍያው እንዲስተካከል ሲል አሻሽሎ የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያጸናው ውሳኔ ተሽሮ ግራ ቀኙ በሚያቀርቡት ክርክርና ማስረጃ ላይ በመመስረት እንዲወስን በማለት የኢፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የሚል የውሳኔ ሃሳብ ቀርቧል፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ያለው ስለሆነ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሙሉ ድምጽ አጽድቋል፡፡

ትዕዛዝ

1. የሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ያቀረቡት የውሳኔ ሀሳብ በምክር ቤቱ ሙሉ ድምጽ ጸድቋል፡፡የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በምክር ቤቱ ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው፡፡
2. የሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ በሙሉ ድምጽ የጸደቀ ስለሆነ እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው፡፡
3. አመልካቾች እነ አቶ ወንድሙ ተሊላ (2 ሰዎች) የሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ በምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ የጸደቀ ስለሆነ እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ይድረሳቸው፡፡

